የመላዉ ኢትዮጲያ አንድነት ድርጅት
All Ethiopian Unity Party (AEUP)

# መኢአድ በመድረክ ዙሪያ ያለውን አቋም አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

መላው የኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ጽ/ቤቶችን ከፍቷል። ጽ/ቤት ባልከፈተባቸው ዞኖችና ወረዳዎች ላይ ደግሞ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ሰፊ የማደራጀት ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል። ሕብረ-ብሔራዊው መኢአድ በሕዝብ ላይ የተጫነውን የገዥዎች ቀንበር በ ምርጫ ካርድ ለማስወገድ በአባላቱና በደጋፊዎቹ ታቅፎ በሰላማዊ መንገድ ሲታገል ቆይቷል። አሁንም በመታገል ላይ ነው።

የመኢአድ አባላት በገዥው ፓርቲ እየደረሰባቸው ያለው ግድያ፣ እስራት፣ ግርፋት፣ ከቤትና ከሥራ መፈናቀል፣ መሰደድና ሌሎችም የመብት ረገጣዎች ሳይፈቷቸውና ሳይበግሯቸው የኢትዮጵያን ትንሳኤ ለማምጣት ተግተው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ከመሰል የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር አብሮ በመስራት የሰው ኃይልን፣ እውቀትን፣ ጉልበትንና ገንዘብን በማስተባበር የተሻለ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል በጽኑ ያምናል።

በዚሁ መሰረትም የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰሞኑን መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ትብብር በኢትዮጵያ (መድረክ) የተሰኘውን ስብስብ አቋም ለማጥናት በተወካዮቹ አማካኝነት ውይይት አካሂዷል። በውይይቱ ወቅትም መኢአድ የመድረክን አቋም ለመገንዘብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አቅርቧል።

ጥያቄዎቹም፡-

- የመድረክ ዓላማና ግቦች ምን እንደሚመስሉ፣
- በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 39 ላይ መድረክ ያለው አቋም ምን እንደሆነ፣
- የተለያዩ ጉሳዎች በተናጠል በፖለቲካ ፓርቲነት በመደራጀትና በሕብረ-ብሔራዊ ፓርቲነት በመደራጀት ላይ መድረክ ያለው አመለካከት

እንዲሁም፣-

- በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት መከበር ላይ የመድረኩ አቋሞች ምን እንደሆኑ ማብራሪያ የሚሹ ነበሩ።

በጥያቄዎቹ መነሻነትም መኢአድ ከመድረኩ ተወካዮች ያገኛቸው ምላሾች ያልተሟሉ መሆናቸውን አንዳንዶቹም መድረክ ገና ወደፊት አቋም የሚይዝባቸው፣ ሌሎቹም ከመኢአድ ዓ ላማ ጋር አብረው ሊጓዙ የማይችሉና የመሳሰሉት ሆነው አግኝቷቸዋል።

በመሆኑም መጋቢት 23 ቀን 2001 ዓ.ም የተሰበሰበው የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በጉዳዩ ላይ በጥልቀትና በስፋት ከተወያየ በኋላ መድረክ አሁን ባለበት የአቋም ደረጃ መኢአድ በአባልነት ተሳታፊ እንደማይሆን በሙሉ ድምጽ ውሳኔ አስተላልፏል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላማዊ ትግል ዲሞክራሲያዊ መብቱን ይቀዳጃል!!

አዲስ አበባ
መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም
የመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ኃይሉ ሻውል
የመኢአድ ፕሬዚዳንት
HAILU SHAWEL
AEUP PRESIDENT